# አማላጅነት በአጸደ ነፍስ

ባለፈው መለከት ቁጥር ፫ መጽሔት ላይ አማላጅነት ከሙቱ ጊዜ ጀምሮ እንደነበር የአማላጅነት ትርጉም ፤ ቅዱሳን በአፀደ ሥጋ እንደሚያማልዱ ፤ እግዚአብሔር የወዳጆቹን ጸሎት እንደሚሰማና የለመኑትን ሁሉ እንደሚፈጽምላቸው . . . አይተናል ። ለዛሬው ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ማማለድ ይችላሉን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት እንሞክራለን ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ያስችለን ዘንድ አስቀድመን የሰውን ተፈጥሮና ከሞት በኋላ የሚገጥመውን ሁኔታ ምን እንደሚመስል ባጭሩ ለመንደርደሪያነት እንገልፃለን ።

እንደሚታወቀው ሰው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ ክቡር ፍጡር ነው (ዘፍጥ. ፩ ፡ ፳፮) ሰው ሥጋው ከምድር አፈር የተሠራ ቢሆንም ሥጋ ብቻ አይደለም ከሥጋ ጋር የተዋሐደች ነፍስ ደግሞ አለችው ። ስለዚህ ሰው በሥጋው የሚራብ ፡ የሚጠማ የሚበላ የሚጠጣ የማይደክም የሚታመም የሚዋለድና የሚሞት ሲሆን በነፍሱ ደግሞ የማይሞት የማይራብ የማይፈርስ የማይበሰብስ አሳቢ (አዋቂ) ተናጋሪ ሕያው ነው ። ሰው ሲሞት ሥጋው ወደተፈጠረበት አፈርነቱ ይመለሳል ይፈርሳል ይበሰብሳል ። ነፍሱ ግን ህያው ስለሆነች እንደሥራዋ ወደ ገነት ወይም ወደ ሲኦል ትሄዳለች ። በዚህ መሠረት ቅዱሳን ሥጋቸው በምድር እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው ሥፍራ ሲቀበር ነፍሳቸው ደግሞ በገነት ውስጥ እንደመላእክት በደስታ ይኖራሉ ። እስከዚህ ድረስ ካየን ደግሞ ጻድቃን በአፀደ ነፍስ ሆነው መለመን ይችላሉን? በምድር የሚደረገውንስ ያውቃሉ. . .? የሚሉትንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ከዚህ በታች ባጭሩ ለመመለስ ተሞክሯል ።

፩/ ከሞት በኋላ ነፍስ የማትሞት ህያው እንደሆነች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ" ( ማቴ. ፲፡ ፳፰ ) "ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ሕያው የሆነው የሚያምንብኝም ለዘለዓለም አይሞትም" (ዮሐ. ፲፩ ፡ ፳፭-፳፮) በተጨማሪ ". . እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር እንድ ወደእናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም" ( ማቴ. ፳፪ ፡ ፴፪ — ፴፫ ) በማለት የሞቱ ቅዱሳን በነፍስ ሕያዋን እንደሆኑ አስረድቶናል ። ከዚህም ሌላ ቅ/ እስጢፋኖስ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል" (ሐዋ. ሥራ ፯ ፡ ፶፱) ሲል ቅ/ ጳውሎስ ደግሞ በአፀደ ሥጋ ከመኖር በአፀደ ነፍስ መኖር የበለጠ እንደሆነ ሲያስረዳ ". . .በእነዚህ በሁለቱ እጨነቃለሁ ልሔድ ከክርስቶስ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ ። ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና ።" (ፊልጵ. ፩ ፡ ፳፪—፳፫) በማለት ጽፏል ።

፪/ ሰው ከሞተ በኋላ በአፀደ ነፍስ እያለ በምድር የሚደረገውን ያውቃል ወይ? ለሚለውና ለሌላውም ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ቃል ፈጣሪያችን በወንጌል ሰጥቶናል ። በሉቃስ ፲፮ ፡ ፲፱—፴፩ ያለውን ጌታችን የተናገረውን ታሪክ ልብ ብለው ያንብቡት በወንጌሉ መሠረት አብርሃም ና አልዓዛር በገነት በደስታ ባለፀጋው ነዌ ደግሞ በሲኦል በሥቃይ በአፀደ ነፍስ እንዳሉ እንረዳለን ።

ሀ/ ባለፀጋው ከሥቃይ የተነሳ አባቴ አብርሃም ሆይ አልዓዛርን ላከውና አንድ ጠብታ ውሃ ይስጠኝ ሲለው አብርሃም ግን በአፀደ ሥጋ ሳላችሁ አንተ መልካም እንደተቀበልህ አልዓዛር ደግሞ ክፉ እንደተቀበለ አስብ አሁንም አንተ ብድርህን ሥቃይ አልዓዛር ዋጋውን ደስታ ተቀብላችኋል በማለት ነግሮታል ። አብርሃም ከሞተ የቆየ ቢሆንም አልዓዛርና ነዌ በምድር ሳሉ በምን ዓይነት ሁኔታ ይኖሩ እንደ ነበር አውቆ እንደተናገረ አስተውሉ ።

ለ/ ባለፀጋው ነዌ ሥቃይ ቢበዛበት በሲኦል ሆኖ ወደአብርሃም ጮሆ እንደለመነና ልመናው ተቀባይነት እንዳላገኘ ከተረዳ በኋላ ተስፋ ቆርጦ ዝም አላለም በምድር ያሉትን ወንድሞቹን አስቦ አባቴ አብርሃም በምድር አምስት ወንድሞች አሉኝና አልአዛርን ወደነሱ ልከህ ወደዚህ ሥቃይ እንዳይመጡ ይንገራቸው በማለት ስለ ወንድሞቹ (እንደለመነ) እንደማለደ እናያለን ባለፀጋው በአጸደ ነፍስ ሆኖ በምድር ስላሉት ወንድሞቹ ማሰቡ ኃጢአተኛም ቢሆን ነፍሱ አዋቂ ስለ ሆነች ወንድሞቹ በንስሐ እንዳልተመለሱ በቀድሞ ኑሮአቸው ያሉ መሆኑን ስላወቀ አይደለምን? ኃጢአተኛው ባለፀጋ ለወንድሞቹ አዝኖ ወደመከራ እንዳይገቡ ከለመነላቸው ቅዱሳን በገነት እያሉ በምድር የሚኖሩ ምእመናን በጸሎትና በትሕትና በፍቅር በአክብሮት ስማቸውን ጠርተው መታሰቢያቸውን በማድረግ ቢለምኗቸው አይረዷቸውም ጨርሶም አይሰሟቸውም ተብሎ እንዴት ይታሰባል?

ሐ/ ባለፀጋው ለለመነው ልመና አብርሃም ኦሪትና ነቢያት አሉላቸው ማለትም መጻሕፍት ተጽፎላቸዋል ሕግ ተሰርቶላቸዋል ብሎ መለሰለት ባለፀጋው ከሙታን አንዱ ቢሄድ ያምናሉ ቢለው ኦሪትንና ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው አያምኑም ማለቱ እስከመጨረሻው ድረስ የሚሠሩትን ቢያውቅ አይደለምን?

፫/ በሉቃ. ፱ ፡ ፳፰—፴፩ በተጻፈው ቃል ጌታችን በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን በገለጸ ጊዜ "ሙሴና ኤልያስ ከጌታ ጋር ይነጋገሩ ነበር በኢየሩሳሌም ሊፈጸም ስላለው ስለመውጣቱ ይናገሩ ነበር" በማለት ያልሞተው ኤልያስና በአፀደ ነፍስ ያለው ሙሴ ጌታ በኢየሩሳሌም ስለሚቀበለው ሕማማተ መስቀል አስቀድመው እንደተናገሩ እናያለን ። ሙሴ በአካለ ነፍስ በክብር ተገልጾ ወደፊት የሚሆነውን መናገሩ ሀብተ ትንቢት እንዳልተነሳውና አዋቂነቱን ያሳያል ።

፬/ ቃየል በቅንዓት ምክንያት አቤልን ቢገድለው እግዚአብሔር ቃየልን "የወንድምህ የደሙ ድምጽ ከምድር ወደ እኔ ይጮኻል ።" በማለት እንደመለሰለት እናያለን (ዘፍጥ. ፬፡፱—፲ ቅዱስ ጳውሎስም በዕብ. ፲፩ ፡ ፬—፭ ላይ " አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መስዋእት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ በዚህም እግዚአብሔር ስለስጦታው ሲመሰክር እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ተመሰከረለት ሞቶም ሳለ እስከ አሁን ይናገራል" በማለት አቤል በነፍሱ እንደ ሚናገር ገልጿል ። ጌታችንም በወንጌል "ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሰዊያው መካከል እስከገደላችሁት እስከበራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ እውነት እላችኋለሁ ።" ( ማቴ. ፳፫ ፡ ፴፭ ) በማለት የቅዱሳን ደም በከንቱ ፈሶ እንደማይቀር ከሞቱ በኋላ እንደሚያስፈርዱ ገልጿል። ለዚህም የአቤልና የሌሎች ቅዱሳን ነፍስ ጠላቶቻቸውን እንዴት እንደተፋረዱ እንመለከታለን በመጽሐፈ ሄኖክ እንደተጻፈው መልአኩ ቅ/ሩፋኤል ለነቢዩ ሄኖክ ነፍሳት ያሉበትን ቦታ እየዞረ ሲያሳየው እንዲህ ብሏል ።

"የደጋግ ሰዎች ልጆች ነፍሳትንም አየሁ እነሱ ሙተው ሳሉ ቃላቸው እስከሰማይ ይደርሳል ወንድሞቻቸውንም ይከሳሉ ያንጊዜም ከእኔ ጋር ያለ ሩፋኤል ቃሉ እስከ ሰማይ ድረስ የሚደርስ የሚከስ ይኸ ነፍስ የማን ነው? ብዬ ጠየቅሁት እሱም ይህ ነፍስ ወንድሙ ቃየል በግፍ ከገደለው ከአቤል የተለየ ነፍስ ነው ። ልጆቹ ከዚህ ዓለም እስኪጠፉ ድረስ የልጅ ልጁም ከሰው ተለድቶ እስኪጠፋ ቃየልን ይከሳል ብሎ መለሰልኝ።" በማለት ያየውን ጽፎልናል (ሄኖክ ፯ ፡ ፳፮ —፳፰) የአቤልና የሌሎችም ነፍሳት በምድር የሚገኙትን ጠላቶቻቸውን ለመበቀል የሚከሱ ከሆነ ይልቁንም ለማዳን ወደፈጣሪያቸው ሊለምኑ አይችሉም ማለት ምክንያታዊ አይሆንም ።

፫ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ከላይ የተጠቀሰውን የመሰለ ጽሑፍ እናገኛለን ። እንዲህ ይላል "አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያው በታች አየሁ ። በታላቅ ድምጽም እየጮኹ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ እስከመቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከመቼ አትበቀልም? አሉ ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው እንደእነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባርያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈጸም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባላላቸው" (ራእይ ፮ ፡ ፱—፲፩) በማለት ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ሄኖክ ያየውን ጽፎልናል ከነዚህ ጥቅሶች የምንረዳው ፡

ሀ/ ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሆነው ወደፈጣሪያቸው መጸለይ (መለመን) እንደሚችሉ የአቤልም ሆነ የሌሎች ሰማእታት ነፍሶች በታላቅ ድምጽ እየጮሁ እንደለመኑ ያሳያል ።

ለ/ ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሆነው በምድር የሚደረገውን እንደሚያውቁ የአቤልም ሆነ የሌሎች ቅዱሳን ነፍሶች ጠላቶቻቸው ጨርሰው እንዳልተፈረደባቸው አሁንም በምድር እንዳሉ አውቀው ፈጣሪያቸው እንዲበቀልላቸው እንደ ለመኑ ለመረዳት ይቻላል ።

ሐ/ ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሆነው የሚለምኑት ልመናቸው ተሰሚ ጸሎታቸው ግዳጅ ፈጻሚ እንደሆነ የአቤል ነፍስ ተካሳ የቃየልን ልጆች በጥፋት ውሃ አስጠፍታለች ። ዮሐንስም ያየቸው የቅዱሳን ነፍስ የለመኑት ልመና ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን እንደ እነሱ አክሊለ ሰማዕት የሚቀበሉ ወንድሞቻቸው ሰማዕታት እስከሚገደሉ ብቻ እንዲታገሱ ከዚያ እንደሚፈረድላቸው ተነግሯቸዋል ። የንጽህና ምልክት የሆነ ነጭ ልብስም አጎናጽፏቸዋል ። እንግዲህ እነዚህ ቅዱሳን ጠላቶቻቸውን ለመበቀል ከጸለዩ የእነሱን ሰማእትነት ለሚቀበሉ በእነሱ ሃይማኖት ለሚያምኑ በጸሎታቸውን ለሚማጸኑ መታሰቢያቸውን ለሚያደርጉ ለሚያከብሯቸው ምእመናን ወዳጆቻቸው ወደ እግዚአብሐር "ማርልን ፣ ይቅር በልልን ከጠላታቸው ከሰይጣን ጠብቅልን ለመንግሥተ ሰማያት አብቃልን . . ." ብለው ለመለመን አይችሉም ። እግዚአብሔርም አይሰማቸውም አይባልም እንግዲህ በማቴ. ፳፫ ፡ ፴፭ ላይ ጌታችን እንደ ጠቀሰው ከአቤል ጀምሮ እስከ ዘካርያስ ድረስ የፈሰሰው የቅዱሳን ደም በዚህ ትውልድ ይፈለጋል ያለው በአፀደ ነፍስ እነዚህ ቅዱሳን ራሱን ጌታችንን አቤቱ እስከመቼ ደማችንን በምድር በሚኖሩት ላይ አትፈርድም ብለው እንደ ጠየቁትና እሱም ልመናቸውን ሰምቶ ፈታሂ በጽድቅ ኰናኒ በርትዕ ነውና እንደሚፈርድ የገለጸው በዚህ ምክንያት ነው (ኢርም ፳፯ ፡ ፲፰ ሄኖክ ፪ ፡ ፴፱—፵) ተመልከቱ ።



፫ ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሆነው በምድር ያሉ ኃጢአተኞችን እንደሚገዙ ጥበበኛው ሰሎሞን በመጽሐፈ ጥበብ "የደጋግ ሰዎች ነፍስ ግን በእግዚአብሔር እጅ ናት የኃጢአተኞች መከራ አላገኛቸውም ላለዋቆች ግን የሞቱ መሰሉ. ሞታቸው ጥፋት መሰለ እነርሱ ግን በተድላ በደስታ አሉ በሰው ፊት ሞቱ ቢባል አለኝታቸው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሞት የሌለበት ፍጽምት ሕይወት ናት" (ጥበብ ፫ ፡ ፩—፬) ብሎ ከጠቀሰ በኋላ "ደግ ሰው ግን ከሞተ በኋላ በደኅንነት ሳሉ እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎችን ይገዛል" (ጥበብ ፬ ፡ ፲፯) በማለት ለቅዱሳን የተሰጣቸውን ክብር ያሳያል ። ነቢዩ ዳዊት ቅዱሳን በአፀደ ሥጋ ሳሉ ኃጢአተኞችን እንደሚገዙ ሲናገር "ቅዱሳን በክብር ይመካሉ በምንጣፋቸውም ላይ ሐሴትን ያደርጋሉ የእግዚአብሔርም ምስጋና በጉሮሮአቸው ነው ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ በእጃቸው ነው በአሕዛብ ላይ በቀልን በሰዎችም መካከል ቅጣትን ያደርጉ ዘንድ ንጉሦቻቸውንም በሰንሰለት አለቆቻቸውንም በእግር ብረት ያስሩ ዘንድ የተጻፈውን ፍርድ ያደርጉባቸው ዘንድ ለቅዱሳን ሁሉ ይህች ክብር ናት ሃሌሉያ" ብሏል (መዝ. ፻፵፱ ፡ ፮—፱ (በምድር እያሉ የተሰጣቸው ፀጋና ክብር በሰማይ በአፀደ ነፍስ ፈተና በሌለበት ድል ካደረጉ በኋላ ክብራቸውየሚጨምር (የሚያበዛ)እንጅ የሚቀንስ አይደለም። በምድር ሳሉ በእግዚአብሔር ኃይል ወደሱ ፀልየው አመፀኞችን የ ፂቀጡ ትሑታን ምዕመናንን የሚረዱ ከሆነ ይህን በአፀደ ነፍስ የማይፈጽሙበት አንዳች ምክንያት የለም። (ከራእይ ፮ ፡ ፱—፲፩ ጋር አነጻጽሩ)

፯' እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ለቅዱሳን ሙታን ሥጋን በተአምራት ሙታን ነፍስን በትምህርት እንዲያስነሱ "ድውዮችን ፈውሱ ሙታንን አስነሱ ፡ ለምጻሞችን አንጹ ፣ አጋንንትን አውጡ . . ." (ማቴ. ፲ ፡ ፰) በማለት ጽኑ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል ። በዚህ መሠረት ነቢዩ ኤልሳዕ በአፀደ ሥጋ ሳለ አንድ ምወት አስነስቷል (፪ ነገሥ. ፬ ፡ ፴፪--፴፯) ኤልሳዕ ስለሞተው ህጻን ወደፈጣሪው አማልዶ (ለምኖ) የህጻኑን ነፍስ ከአፀደ ነፍስ አምጥቶ በአፀደ ሥጋ ከሚገኘው አስከሬን ጋር በማዋሐድ አስነስቶታል ። ይኸው ነቢይ ኤልሳዕ ከሞተም በኋላ በአፀደ ነፍስ ሆኖ ተመሳሳይ ሥራ ሠርቷል ። "ኤልሳዕም ሞተ ቀበሩትም ከሞዓብም አደጋ ጣዮች በየዓመቱ ወደ አገሩ ይገቡ ነበር ሰዎችም አንድ ሰው ሲቀብሩ አደጋ ጣዮችን አዩ ። ሬሳውንም በኤልሳዕ መቃብር ላይ ጣሉት ። የኤልሳዕንም አጥንት በነካ ጊዜ ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ ።" ( ፪ ነገሥ ፲፫ ፩ ፳፩ ) ይላል ። ኤልሳዕ በኤልያስ ያደረው ሀብተ መንፈስ ቅዱስ እጥፍ ድርብ ሆኖ እንደተሰጠው ለሚጠየቅ ኤልያስ አንድ ምውት ሲያስነሳ ኤልሳዕ ግን ሁለት ምውት አንዱን በአፀደ ሥጋ ሳለ ሁለተኛውን ግን በአፀደ ነፍስ እያለ አስነስቷልውጤቱ ማለትም የሞቱት ሰዎች መነሳት አንድ ሲሆን ኤልሳዕ በአፀደ ሥጋ ሆኖ የሠራውን ከሞተ በኋላም ያንኑ ተመሳሳይ ሥራ መሥራቱ ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ቢለምኗቸው አይረዱም የሚለውን ሐሳብ ውድቅ ያደርገዋል ።

፰/ በመጀመሪያ ታሪኩን ለመረዳት ፩ ነገሥ. ፲፫ ፡ ፩—፴፪ ያለውን በደንብ ያንብቡት ። በታሪኩ መሠረት በቤቴል መሠዊያ ላይ ትንቢት የተናገረውን ነቢይ በሐሰት ያሳሳተውና ያስቀሰፈው ሽማግሌው ነቢይ የነቢዩን አስከሬን ወደገዛ ከተማው አምጥቶ በራሱ መቃብር ቀበረው አለቀሰለትም በመጨረ

ሻም ሸማግሌው ነቢይ ልጆቹን ሰብስቦ "በሞትሁ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው (በቤቴል ትንቢት የተናገረው ነቢይ) በተቀበረበት መቃብር ቅበሩኝ አጥንቶቼንም በአጥንቶቹ አጠገብ አኑሩ በቤቴል ባለው መሰዊያ ላይ . . . በእግዚአብሔር ቃል የጮኸው ነገር በእውነት ይደርሳልና ።" በማለት ተናዘዘ ይህ ሽማግሌ ነቢይ ይህን መናዘዙ በሐሰት ያሳሳተው ነቢይ እውነተኛ መሆኑን አውቆ በፈጸመው ኃጢአት በአካለ ነፍስ እንዲረዳው አይደለምን? ቅዱሳን ከተቀበሩበት ቦታ የሚቀበር ከቅዱሳን ረድኤት በረከት እንደሚሳተፍ የኤልሳዕና የዚህ ነቢይ ታሪክ አስረጅ ነው ። ስለቅዱሳን ሰዎች መቃብር በተመለከተ ነቢዩ ዳዊት "የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል እግዚአብሔር አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል ከእነርሱም አንድ አይሰበርም" (መዝ. ፴፫፥ ፲፱—፳) በማለት እግዚአብሔር ከቅዱሳን መቃብር እንደማይለይ ተናግሯል ። ስለዚህ ቅዱሳን ከተቀበሩበት ቦታ መቀበር እንደሚያስጠቅም ጉልህ ማስረጃ ነው ። ዛሬም ቅዱሳን ከተቀበሩበት ቦታ ለምሳሌ ደብረ ሊባኖስ ወስዳችሁ ቅበሩኝ በማለት ብዙ ሰዎች የሚናዘዙትና በኑዛዜው መሠረት የሚቀበሩት ከላይ በተጠቀሱት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ላይ በመመሥረት እንጅ በልማድ አይደለም ። ደግሞም የጻድቃን ብሉይ መቃብር ይህን ያህል ከጠቀመ የጻድቃን ሐዲስ መቃብርማ አብልጦ እንዴት አይጠቅም ።

፱/ በኤርምያስ ፲፭ ፥ ፩ ላይ "እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ ሙሴና ሳሙኤል በፊቴ ቢቆሙም ልቤ ወደ ዚህ ሕዝብ አያዘነብልም ከፊቴ ጣላቸው ይውጡ ።" በማለት ጽፎአል ሙሴና ሳሙኤል በአፀደ ሥጋ ሳሉ ለወገኖቻቸው ያማልዱ እንደነበር ታሪካቸው ያስረዳል ። እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ስለጸኑ ኤርምያስም ቢጸልይላቸው እግዚአብሔር "አልሰማህም ና አትፀልይላቸው!!" እንዳለው በኤር፣ ፯ ፥ ፲፯—፳ ተጽፎአል ። ኤርምያስ በአፀደ ሥጋ ስለወገኖቹ ሲፀልይ ሙሴና ሳሙኤል በአፀደ ነፍስ ሆነው እንደሚፀልዩ ጥቅስ ያስረዳል ። "በፊቴ ቢቆሙም" የሚለው አባባል ቢጸልዩም ፣ ቢለምኑም ፣ ቢማልዱም ማለት እንደ ሆነ ዳዊት በመዝሙሩ ". . . ያዳናቸውንም እግዚአብሔርን ረሱ እንዳያጠፋቸውም ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ።"(መዝ. ፻፭፥፳፩—፳፫) በማለት ሙሴ በኦሪት ዘጸአት ፴፪ ፥ ፩—፲፬ ላይ ያለውን እስራኤላውያንን በጸሎቱ ከመቅሰፍት ያዳነበትን ታሪክ ገልጾታል ። በዚህ መሠረት ሙሴ በአፀደ ነፍስ ከሳሙኤል ጋር እንደሶመደው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳይቀስፍ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ይጸልይ ነበር ማለት ነው ።

፲/ የእስራኤል ንጉሥ ሳዖል ፍልስጥኤማውያን ከበውት በተጨነቀ ጊዜ ወደፈጣሪው ጸለየ እግዚአብሔርም በሕልምም በነቢይም ቢሆን አልመለሰለትም ። ስለዚህ በተጨነቀ ጊዜ በዓይንዶር ወዳለች አንዲት ሴት ሄዶ የነቢዩ ሳሙኤልን ነፍስ እንድትጠራለት ጠየቃት ። (ታሪኩን ፩ ሳሙ. ፳፰ ፥ ፫—፳፭ ይመልከቱ) እሷም በተባለችው መሠረት ሳሙኤልን ጠርታ ባየችው ጊዜ ደነገጠች "አንድ ሽማግሌ ሰው ወጣ መጎናጸፊያም ተጎናጽፎአል" አለች ሳዖልም ሳሙኤል እንደሆነ አውቆ በምድር ላይ ተንጉብሶ እጅ ነሳው ሳሙኤልም ሳዖልን "ለምን አወከኸኝ ለምንስ አስነሳኸኝ አለው "ሳዖልም "እነሆ ፍልስጥኤማውያን ከበውኛል እጅግ ተጨንቄአለሁ እግዚአብሔርም አልመለሰልኝም ከእኔ ርቋል አለው ።" ሳሙኤልም እግዚአብሔር በቃሌ እንደተናገረ እንዲሁ መንግሥትህን

ከአንተ ወስዶ ለዳዊት ሰጥቶታል በአማሌቅ ላይ ያለውን ታላቅ ቁጣውን አላደረግህምና እስራኤላውያንን ከአንተ ጋር አሳልፎ ይሰጣል አንተና ልጆችህ ነገ ከእኔ ጋር ትሆናላችሁ ።" በማለት ወደፊት የሚደርስበትን ሁሉ ነገረው።ከዚህ የምንረዳው በዘመነ ኦሪት በዓመተ ፍዳ በዓመት ኩነኔ የነበረ ሳሙኤል በአካለ ነፍስ ተገኝቶ ካነጋገረውና የሚደርስበትን ነገር አስቀድሞ ከሳወቀው ያም ከተፈጸመ በዘመነ ሐዲስ በዓመተ ምሕረት በገነት ያሉ የቅዱሳን ነፍሳት በተጨነቅን ጊዜ በጸሎታቸው አምነን በቃልኪዳናቸው ተማጽነን ብንጠራቸው በአካለ ነፍስ በረድኤት እንደሚገኙንና ከችግራችን እንደሚታደጉን ለእኛ ለኦርቶዶክሳውያን ጥርጥር የሌለበት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ሁልጊዜ የምናረጋግጠው እውነተኛ ቃል ነው ።

፲፩/ በማቴ. ፲፱ ፥ ፳፯— ፴ ላይ ቅዱስ ጴጥሮስ "እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከትለንህ እንከየስ ምን እናገኝ ይሆን "ብሎ ጌታን ጠየቀው ጌታችንም "እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአስራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ" በማለት በአፀደ ሥጋና በአፀደ ነፍስ የሚያገኙትን ክብር ገልጾላቸዋል ። እንግዲህ በአሥራ ሁለት ወንበር ተቀምጠው እንዲፈርዱ ሥልጣን ከሰጣቸው ለምና ማስታረቅን ይቅርታን ማስጠትን ይነፍጋቸዋል ተብሎ አይታሰብም ከማማለድ ይልቅ መፍረድ ይበልጣልና ።

በመጨረሻ ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሳሉ በቀደመ ልመናቸው (በአፀደ ሥጋ እያሉ በጸለዩት ጸሎት) እንደሚያማልዱ ስለ ቃል ኪዳን ዝክርና ተዝካር በሚቀጥለው እትም ለማቅረብ እንሞክራለን እግዚአብሔር በወዳጆቹ ጸሎት በእናቱ አማላጅነት በቸርነቱ ያርዳን አሜን ።

# አማላጅነት በአጸደ ነፍስ

(ካለፈው የቀጠለ )

ባለፈው ወር በቁጥር ፩ ላይ ሰው በነፍሱ ሕያው አዋቂ ነባቢ እንደሆነና ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ ሳሉ መለመን ማማለድ እንደሚችሉ ሲጠሩዋቸው እንደሚሰሙ ለመግለጽ ተሞክሯል ። ቀጣዩን ከዚህ በታች እንጽፋለን።።

ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ ሆነው እንደሚያማልዱ መልአከ ገነት ጽጌ ሻውል የተባሉ የቤተክርስቲያን ሊቅ አንዱን ተከራካሪ ያሳፈሩበትን ታሪክ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. ከታተመ "መርሐ ምእመናን" ከተባለ መጽሔት ያገኘነውን ጽፈናል ።

"በሊቅነታቸው የታወቁት መልአከ ገነት ጽጌ ሄኖክ ጻድቃን ለሰው ልጆች እግዚአብሔርን ይለምናሉ ያማልዳሉ ይጸልያሉ ብሎ የተናገረውን ቃል መሠረት በማድረግ ጻድቃን ሰማዕታት እያማልዱም እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አታማልድም እያለ ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር ይከራከር የነበረውን መናፍቅ እንዲህ ብለው ተከራክረው ረትተውታል ።

"መጀመሪያ ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ ትቀበለኛለህን! ብለው ቢጠይቁት አዎን ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ እቀበልሐለሁ ብሎ መልሶላቸዋል ። ለጊዜው ክርክርና ሙግት ሁሉ የሚወስነው ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ሁሉ ክሱ በሚበልጥ ይምላል ክርክርም በመሐላ ይፈጸማል እንዳለ እንደ ቀድሞው ልማድ ምኒልክ ይሙት እያሉ የንጉሥን ስም በመጥራት ነበርና ማን ይሙት ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ ትቀበለኛለህ? ብለው ሁለተኛ ቢጠይቁት ምኒልክ ይሙት ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ እቀበልሐለሁ ብሎ የመጨረሻ ቃሉን ከሰጣቸው በኋላ ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ ከተቀበልከኛማ ሐዋርያት የተቀበሉት መጽሐፈ ሄኖክ ጻድቃንና ሰማዕታት በሞት ካረፉ በኋላ ስለሰው እንደሚያማልዱ ሲያስረዳ 'ጻድቃን ይሰእሉ ወያስተበቁዑ ወይጼልዩ በእንተ ውሉደ ሰብእ ወጽድቅ ከመማይወንዝ በቅድሚሆሙ' (ትርጉም) 'ጻድቃን ስለሰው ልጆች ይለምናሉ ጽድቅም በፊታቸው እንደውሃ ይፈሳል' ብሏል ። ቀጥሎም 'ሕያዋን ይሰእሉ በእንተ ሙታን ወሙታን ይሰእሉ በእንተ ሕያዋን' (ትርጉም) ሕያዋን ስለሙታን ይለምናሉ ሙታንም ስለሕያዋን ይለምናሉ ።' ብሎ ማማለዳቸውን ተናግሯል ። ሄኖክ ፲፪ : ፴፫—፴፮ ሄኖክ ፱ : ፳፫ ። ፳፬ 'መጽሐፈ ሄኖክ ሐዋርያት የተቀበሉት ለመሆኑ ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ :— እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ በኃጢአተኞችም ስላደረጉት ስለ ኃጢአተኛ ሥራቸው ሁሉ ዓመፀኞችም ኃጢአተኞች በእርሱ ላይ ስለተናገሩ ስለጭካኔ ነገር ሁሉ ኃጢአተኞችን እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር ይመጣል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ" በማለት ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ቢጽ ሐሳውያንን በሚወቅስበት ጊዜ ቃሉን ጠቅሶት ይገኛል የሄኖክን መጽሐፍ ሐዋርያት አልተቀበሉትም እንዳትለኝ እንደተቀበሉት ይኸው አስረዳሁህ ። ሐዋርያት የተቀበሉትን መጽሐፍ እቀበላለሁ ስትል ምኒልክ ይሙት ብለህ ከተፈጠምክ ሐዋርያት የተቀበሉት መጽሐፈ ሄኖክ ሙታን ለሕያዋን እንደሚያማልዱ ጽፎ ከተገኘ ተረታህ ቢሉት የሚመልሰው ኃይለ ቃል በማጣቱ መረታቱ ተረጋግጦበት ሄዷል ። (ይሁዳ ፩ : ፲፬ : ፲፭ ሄኖክ ፩ : ፱)

ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት በአጸደ ነፍስ ያማልዳሉ ስንል ግን ልክ በአጸደ ሥጋ ሲያማልዱ እንደነበረው በጾም በእንባ ልዩ ልዩ ጻዋትወ መከራ በመቀበል ሳይሆን በምድር ሳሉ የለመኑት ልመናና የተቀበሉት ቃል ኪዳን ለዘላለም በእግዚአብሔር ዘንድ ሕያው ስለሆነ በተሰጣቸው ቃል ኪዳን ስለሚያስምሩ ነው። ይህን በተመለከተ በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ "ስአሊ ለነ ቅድስት" (ትርጉም) "ቅድስት ሆይ ለምኝልን" የሚለውን ጸሎት ሊቃውንቱ ሲተረጉሙት "...እንኳን በእሷ በሌሎችም ልመና የለባቸውም በቀደመ ልመናዋ የምታስምር ስለሆነ እንዲህ አለ እንጂ " ብለው ተርጉመውታል ። ስለዚህ እመቤታችን በአጸደ ሥጋ ሳለች የጸለየችው ጸሎት የተቀበለችው ቃል ኪዳን ሕያው ስለሆነ በዚያ ቃል ኪዳን አምኖ ለሚጸልይ ሁሉ የበረከቱ ተሳታፊ ይሆናል ።

# ቃል ኪዳን

እግዚአብሔር ይህን ዓለም የሚያስተዳድረው በቃል ኪዳን ሥርዓት ነው ። ስለሆነም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በርካታ ኪዳኖች ተጽፈው እናገኛለን ። እግዚአብሔር በጥቅሉ ለመላው የሰው ዘርም ቢሆን ወይም ለተለዩ ለተወሰኑ ወዳጆቹም ቢሆን ቃል ኪዳን ይገባል ። እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሲገባ ለዚያ ቃል ኪዳን ተፈጻሚነት መሟላት ያለባቸው አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ይደ ልጻል ። እንዲሁም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ቃል ኪዳን የሚገባበት ጊዜም አለ ። እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሲገባ ተናግሮ የማያስቀር ምሎ የማይክድ እውነተኛ አምላክ ሲሆን ቃል ኪዳኑ ጽኑ እንደሆነ ለማጠየቅ በመሐል የሚ ጸናበት ጊዜም አለ ።

እግዚአብሔር አንዴ ቃል ኪዳን ከገባ በኋላ ያንን የገባውን ቃል ኪዳን አይዘነጋውም ሁሌም ያስበዋል ። በዚህ መሠረት ያንን ቃል ኪዳን አምነው አሳስበው ለሚለምኑ ሰዎች በዚያ ቃል ኪዳን ውስጥ የተሰጠው ተስፋ ያደረግላቸዋል ። እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሲገባ የቃል ኪዳን ምልክት ሊሰጥ ይችላል ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን በሚከተሉት ጥቅሶች መገንዘብ ይቻላል ።

ሀ. እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ በገነት ካኖራቸው በኋላ "ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን

መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ'' ብሎ በሾመው ጊዜ ከሰው ሁሉ ጋር የተፈጥሮ ቃል ኪዳን ተጋብቶ ነበር ። አዳምና ሄዋን ይህንን ቃል ኪዳን ቢጠብቁ ኖሮ ሞትን አይሞቱም ነበር። ነገር ግን ቃል ኪዳኑን ባለመጠበቅ ሞት ተፈረደባቸው (ዘፍጥ. ፪ ፣ ፲፯ ሆሴዕ ፮ ፡ ፯)

፪. አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ በኃጢአታቸው ተጸጽተው ንስሐ ገብተው ሲለምኑት (መቃ. ፬ ፳፬—፳፰) መሐሪ ወመስተሣህል እግዚአብሔር ''በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ . . . ወእቤዝወከ በመስቀለ ሞትየ'' (ትርጉም) ''ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በሜዳህ ድሐ ተሰቅየ በሞቴ አድንሐለሁ'' በማለት ለአዳምና ለዘሩ ጽኑ ቃል ኪዳን ገባለት ። (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ተመልከቱ) በዚህ ቃል ኪዳን መሠረት ከ፭ሺህ፭፻ ዘመን በኋላ ወልደ እግዚአብሔር ከእመቤታችን ተወልዶ አድኖናል ። ይህም ኪዳነ አዳም ይባላል ።

፫. በኖህ ዘመን እግዚአብሔር ዓለምን በጥፋት ውሃ አጥፍቶ ጻድቁን ኖህን ከነቤተሰቡ ካዳነው በኋላ ኖህ መሥዋዕት ቢሰዋ መስዋዕቱን ተቀብሎ ለመላው የሰው ዘር የሚሆን ቃል ኪዳን ሰጠው ''እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ . . . ሥጋ ያለውም ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውሃ አይሆንም'' ብሏል ። (ዘፍጥ. ፰ ፣ ፳ ፡ ፳፩ ዘፍጥ. ፱ ፣ ፰ - ፲፯) የቃል ኪዳንም ምልክት የሚሆን ደመና በዘረጊዜ ቀስተ ደመናን እንደሚያደርግ ቃልኪዳኑንም ለማሰብ ያችንም ቀስተ ደመና እንደሚመለከት በቁ. ፲፮ ፣ ፲፯ ላይ ተጽፎ ይገኛል ። ይህ የምህረት ቃል ኪዳን ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ ያልቀረበበትና እስከዓለም ፍጻሜ ለሚነሳ ትውልድ ሁሉ ተፈጻሚ የሚሆን ነው ይህ ደግሞ ኪዳነ ኖኅ ይባላል ።

፬. እግዚአብሔር በተፈጥሮ ሰው ሁሉ የሱ ገንዘብ ሲሆን ከሰው ለይቶ መርጦ ለሚወዳቸው ባለሟሎቹ ቃል ኪዳን ይገባል ። እግዚአብሔር ከሌላው ለይቶ ለመረጣቸው ለወዳጆቹና ለባለሟሎቹ ቃል ኪዳን እንዲደሚገባ ''ኪዳነ ተካየድኩ ምስለ ኅሩያንየ'' (ትርጉም) ''ከመረጥኳቸው ጋራ ቃል ኪዳን አደረግሁ ።'' በማለት ከኃጥአን ለይቶ ለጻድቃን ፣ ከርኩሳን ለይቶ ለቅዱሳን ፡ ከህጹጻን ለይቶ ለፍጹማን እንደፈቀዱ ቃል ኪዳን እንደሚገባ ቅዱስ ዳዊት ገልጿል ። (መዝ. ፹፰ ፡ ፫ ግዕዙን ይመልከቱ) ከዚህም ሌላ ነህምያ ''አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ ለሚወዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንና ምህረትን የምትጠብቅ ታላቅና የተፈራህ የእስራኤል አምላክ ሆይ . . .'' (ነህ ፩:፬—፭) ብሏል።ንጉሡ ሰሎሞንም ደግሞ እንደዚሁ ''አቤቱ የእስራኤል አምላክሆይ በሰማይ ወይም በምድር አንተን የሚመስል አምላክ የለም በፍጹም ልባቸው በፊትህ ለሚሄዱ ባሪያዎችህ ቃል ኪዳንና ምህረትን የምትጠብቅ ለባሪያህ ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸውን ተስፋ የጠበቅህ'' (፪ ዜና ፮ ፡ ፲፬ - ፲፭) በማለት እግዚአብሔር ለቅዱሳን ወዳጆቹ ከሌላው ለይቶ ቃል ኪዳን እንደሚገባና ቃሉንም እንደሚፈጽም ገልጾአል ።

ውለታሽ ብዙ ነው ማርያም እናቴ
አትብልችኝ ታዲያ እማማ በሞቴ፣
ስኔ ብለሽ ነው ያሁሉ ችግር ፣
እንዳውቅ እንድማር ።
ሁሉም ቢሰሚት ምነው ፡
የድንግል ምክር ጠቃሚ ነው ፡
ሁልጊዜም ሌላ አትመክሩ ፣
ተማር ተማር ተማር !
ባለጠጋ ነው አሉ እጅጉን ፡
የድንግል ልጅ የሚረዳ ሁሉን ፡
ምንድን ነው የሱ ብልጥግና ፣
አታርፍ እናቴ ክልመና ።
ሞልቶ ተርፎ የልጅዋ ሀብት ፣
ማርያም ስትለምን እይዋት ፣
የፍጥረት ሁሉ ትካዜ
ያስለምናታል ሁልጊዜ ።

፭. በዚህ መሠረት ሰው ሁሉ በአምልኮ ጣዖት በተያዘበት ጊዜ አብርሃም ብቻ በአምልኮተ እግዚአብሔር ጸንቶ ቢገኝ ከሰው ለይቶ ጽኑ ቃል ኪዳን ገባለት። ይህንንም ቃል ኪዳን የገባለት መጻተኛ በሆነበት ልጅ ባልወለደበት ወቅት ነበር ። በዘፍጥ. ፲፭ ፣ ፭ ላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር አብርሃምን ''ወደሜዳ አወጣውና ወደሰማይ ተመልከት ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር አለው ። ዘርህም እንደዚሁ ይሆናል አለው'' ይላል በዚሁ ምዕራፍ በቁ. ፲፰ ላይ ''ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህንን ምድር ለዘርህ ሰጥቼ አለሁ'' በማለት ዘርና ርስት እንደሚሰጠው ቃል ኪዳን ገባለት ይህንኑ ቃል ኪዳን በማጽናት በድጋሚ በዘፍ. ፲፯ ፡ ፯—፰ ላይ ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው የዘለዓለም ቃል ኪዳን አቆማለሁ በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር የከነዓን ምድር ሁሉ ለዘለዓለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ አምላክም እሆናቸዋለሁ'' ካለ በኋላ የቃል ኪዳን ምልክት የሚሆን ግዝረትን ሠራላቸው ። ''በእኔና በአንተ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ የቁልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ በእኔና በአንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል ። የቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘ ቆላፍ ሰው ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና'' በማለት የቃል ኪዳኑን ጽናት ገልጿል ። (ዘፍጥ. ፲፭ እና ዘፍጥ. ፲፯ በሙሉ ይመልከቱ) ይህም ኪዳነ አብርሃም ይባላል ።

፮. ይህንንም ቃል ኪዳን እግዚአብሔር ለአብርሃም ከኬጡራ ከተወለዱት ፮ ልጆችና ከአጋር ከተወለደው ከእስማኤል ለይቶ ከሣራ ለተወለደው ለይስሐቅ አጽንቶ ምሎለታል ። ቃል ኪዳኑም ''. . .በዚችም ምድር ተቀመጥ ከአንተ ጋርም እሆናለሁ እባርክሀማለሁ እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁና ለአባትህ ለአብርሃም የማልሁለትንም መሐላ አጸናለሁ ። ዘርህንም እንደሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ ። የምድርም አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ አብርሃም ቃሌን ሰምቶአልና ፍርዴን ትእዛዜን ሥርዓቴን ሕጌንም ጠብቆአልና'' የሚል ነበር (ዘፍጥ. ፳፮ ፡ ፩—፭)

፯. ከይስሐቅም በኋላ በአንድ ዕለት ከተወለዱት ከኤሳው ለይቶ ለያዕቆብ አጽንቶለታል ። ያዕቆብም በመጀመሪያ በፍኖተ ሎዛ ሌሊት በራእይ እግዚአብሔር ተገልጦለት ቃል ኪዳን እንደገባለት በዘፍጥ. ፳፰ ፤ ፲—፲፭ ተገልጿል። እግዚአብሔር ለያዕቆብ በሁለት ወንዞች መካከል ከሶሪያ ከተመለሰ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ተገልጦለት ስሙን እስራኤል ብሎ እንዳወጣለትና "... ለአብርሃምና ለይስሐቅ የሰጠኋቸውን ምድር ለአንተ እሰጣለሁ ከአንተም በኋላ ለዘርህ ምድሪቱን እሰጣለሁ ..." በማለት ቃል ኪዳኑን አጽንቶለታል ። (ዘፍጥ. ፴፭ ፡ ፱—፲፫)

፰. እግዚአብሔር ከአሕዛብ ለይቶ ለእስራኤል ብቻ ሕግ እንደሠራላቸውና ቃል ኪዳን እንደገባላቸው በዘጸአ. ፳ ፡ ፩—፳፮ የተገለጸውን መመልከት ይቻላል (ዘዳግ. ፳፱ ፡ ፩) እግዚአብሔር በሚያስፈራ ሁኔታ ተገልጾ የቃል ኪዳኑን ሕግ ከሰጣቸው በኋላ ያንን ሕግ አክብረው ቢጠብቁ በሕይወት በበረከት እንደሚኖሩ ሕጉን ባያከብሩ ቅጣት እንደሚደርስባቸው ተገልጿል (ዘዳግ. ፴ ፡ ፲፭-፳) በዚህም ምክንያት የጽላቱ መቀመጫ ታቦት የቃል ኪዳን ታቦት ይባላል ። (ዘዳግ. ፲ ፡ ፰ ኢያሱ ፤ ፡ ፤ ፡ ፫ ፩ ነገሥ. ፫ ፡ ፳፩) በዘጸአ ፳ ላይ ከተጠቀሱት ትዕዛዛት መካከል ቁ. ፭—፮ ያለው "... በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና" በማለት ለወዳጆቹ ይህን የመሰለ ታላቅ የምህረት ቃል ኪዳን መስጠቱን ገልጿል ።

፱. እስራኤላውያን ከሞዓባውያን ጋር ስላመነዘሩና ለአማልክቶቻቸው ስለሰገዱ እግዚአብሔር በጣም አዘነ ። አንዱ እስራኤላዊ ይባስ ብሎ አንዲቱን ሴት ይዞ በመገናኛው ድንኳን አካባቢ ጸያፍ ሥራ በሰራ ጊዜ የካህኑ የአልአዛር ልጅ ፊንሐስ ቀንቶ በጦር ሁለቱንም ስለወጋቸው ከእስራኤል ልጆች መቅሰፍቱ ተከለከለ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር "የካህኑ የአሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በቀንዓቴ በመካከላቸው ቀንቶአልና ቁጣዬን ከእስራኤል ልጆች መለሰ እኔም የእስራኤልን ልጆች በቅንዓቴ አላጠፋሁም ስለዚህ እነሆ የሰላሜን ቃል ኪዳን እሰጠዋለሁ ለአምላኪም ቀንቶአልና ለእስራኤልም ልጆች አስተስርዮአልና ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ለዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን ይሆንለታል ። " (ዘኁል. ፳፭ ፡ ፲- ፲፫) በማለት ለአምላኩ ሕግ በመቅናቱ ከእርሱ አልፎ ለዘሩ የሰላምና የክህነት ቃልኪዳን እንደተሰጠው እናያለን ። እንደዚህ ዓይነት ቃል ኪዳን በፊንሐስ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን በዘጸአ ፳ ፡ ፮ ላይ እንደተጠቀሰው "ለሚወዱትና ትእዛዙን ለሚጠብቁ ሁሉ እስከ ሺህ ትውልድ ምህረትን" እንደሚያደርግ ግልጽ ነው ።

፲. እግዚአብሔር ዳዊትን ከወንድሞቹ መርጦ ካነገሠው በኋላ ከነገሥታት ለይቶ መንግሥት ከ[ሩ እንዳይወጣ ጽኑ ቃል ኪዳን ገባለት "ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ ፡— ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ" ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት እጄም ትረዳዋለች ክንዴም ታጸናዋለች ..." (መዝ. ፹፰ ፡ ፫—፬ ፡ ፳—፴፯ ይመልከቱ) በተጨማሪ "እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ አይጸጸትምም እንዲህ ብሎ ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ ልጆችህ ኪዳኔን ይህንም የማስተምራቸውን ምስክሬን ቢጠብቁ ልጆቻቸው ደግሞ በዙፋንህ ላይ ለዘላለም ይቀመጣሉ ።" በማለት በመሐላ ቃል ኪዳኑን አጽንቶለታል ። በዚህ መሠረት በአባት ቃል ኪዳን ልጆች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መረዳት ይቻላል ። በዚህ ኪዳነ ዳዊት መሠረት ከሰሎሞን ጀምሮ በመንበረ ዳዊት የተቀመጡትን ልጆቹን ከቅዱሳት መጻሕፍት ማግኘት ይቻላል ።

፲፩. በአዲስ ኪዳን ደግሞ ከላይ ለተጠቀሱትና ላልተጠቀሱት ቅዱሳን ወዳጆቹ ቃል ኪዳን የሰጠ እግዚአብሔር በኋላ ዘመን ራሱ በሥጋ ድንግል ማርያም ተገልጾ በሚያስተምርበት ወቅት ላለፉትም ወደፊትም ለሚመጡት ወዳጆቹ የሚሰጠውን የቃል ኪዳን ክብር እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደሸማ ጠቅሎ በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. ፲ ፡ ፵—፵፪ ላይ አስቀምጦታል ። ይህ ለጻድቃን ሐዲስ በጠቅላላ የተሰጠ የቃል ኪዳን ሁሉ መሠረት ነው ። ቃሉም በግዕዝ "ዘኪያክሙ ተወክፈ ኪያየ ተወክፈ ፤ ወዘኪያየ ተወክፈ ተወክፎ

## እንጠይቃችሁ

፩/ ከ፹ አሀዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ምዕራፍ ብቻ ያላቸውን መጻሕፍት ይጻፉ ።
፪/ የእመቤታችንን "አምስቱ ሀዘናት" ከቅዱስ ወንጌል ጥቅስ ጋር በማዛመድ ይጻፉ ።
፫/ ጌታችን በመስቀል ላይ ሆኖ የተናገራቸውን "ሰባቱን አጽርሐ መስቀል" ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልገው ንባቡን ከነጥቅሱ ይጻፉ ።
፬/ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፦
ሀ/ የትውልድ ሀገርና ሥፍራ ፣ ለ/የአባታችውና የእናታቸው ስም ሐ/ የተወለዱበትና ያረፉበት ዕለት መ/ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡና ጠቅላላ እድሜአቸው ስንት እንደሆነ አጠር አድርገው ይጻፉ ።
፭ የሚከተሉትን ጥቅሶች በታቸውን ይጻፉ ፡—
ሀ/«ጀርባዬን ለገራፊዎች ጉንጬን ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስሁም»
ለ/ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ»
ሐ/«የባሕርይ አምላክ ክርስቶስን ኑ እንግደለው አሉ »

ለዘፈነወኒ።ወዘተወክፈ ነቢየ በስመ ነቢይ አስበ ነቢይ ይነስእ፣ ወዘተወክፈ ጻድቀ በስመ ጻድቅ ዓስበ ጻድቅ ይነስእ። ወዘ አስተየ ለአሀዱ እምእሉ ንዑሳን ጽዋዓ ማይ ቆሪር ባሕቲቱ በስመ ረድእየ አማን እብለክሙ ኢየኃጉል ዓስቦ'' (ትርጉም) ''እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢዩን ዋጋ ይወስዳል ። ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙሬ ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።'' ይላል ። ይህ በወንጌል ያለ ሲሆን ለሐዋርያትም ሆነ ከነሱ በኋላም ለተነሱ ቅዱሳን ''ዘጸውዐ ስመከ ወዘገብረ ተዝካረከ እምህር ለከ'' (ትርጉም) ''ስምህን የጠራውን መታሰቢያህን ያደረገውን እምርልሃለሁ'' ለሚለው የምህረት ቃል ኪዳን ጥንቱ መሠረቱ መነሻው ይህ ምንጩ ከላይ በወንጌል የተጠቀሰው የጌታ ቃል ነው ።

ከዚህ ቀደም ብለን እንደጠቀስ ነው እግዚአብሔር ለመረጣቸው ፤ ለወደዳቸው በሕጉ በትዕዛዙ ለሚሄዱ ምርጦቹ ሁሉ ቃል ኪዳን እንደሚገባ (በዘፍጥ. ፳ ፡ ፯ በመዝ. ፹፰ ፡ ፫ በ፪ ዜና ፮ ፡ ፲፬ . . .) ጠቅሰናል ። ከወዳጆቹ መካከል በተለይ ለአዳም ለኖህ ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብና ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን አይተናል ። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሱ የእግዚአብሔር ወዳጆች እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ እጅግ ብዙ ናቸው። የነዚያ ሁሉ ቃል ኪዳን ቢጻፍ ምን መጽሐፍ ይችለው ነበር? በሐዲስ ኪዳንም እንዲሁ እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሱት ሁሉ አንዴ አጠቃሎ ቃል ኪዳን ከገባ በኋላ አንዱ ጻድቅ ወይም ሰማዕት ዕረፍቱ ሲደርስ ከወንጌሉ ቃል ጋር የማይጋጭ የወንጌል ፍሬ የሆነ ቃል ኪዳን እንደጻድቁ ክብርና ትሩፋት ቃል ኪዳን ይሰጠዋል ። ይህ ቃል ኪዳን በጻድቁ የገድል መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ ሰው ያነበዋል ። በዚህም የጻድቁን ክብር የእግዚአብሔርን ፍቅር የጻድቁን ትሩፋት የፈጣሪን ቸርነት በመገንዘብ መታሰቢያውን ለማድረግ እንተጋለን ። ለኦርቶዶክሳውያን ይህ ድንቅ እንጂ ጭንቅ አይሆንብንም ።

፲፱ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ለአገልጋዮቹ ሰው ስማቸውን ጠርቶ መታሰቢያቸውን አድርጐ እንዲድን ከፈቀደ ፤ ከፍጥረት ሁሉ አልቆ አክብሮ አግኖ ቀድሶ ለፈጠራት ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ለከበረች እናቱ ቃል ኪዳን አይገባላትም ብሎ የሚያስብ ሕሊና ምን ዓይነት ሕሊና ነው? ነቢያት ለተነበዩላት ፣ ምሳሌ ለመሰሉላት ሱባዔ ለቆጠሩላት ፣ አዳምና ልጆቹ ሁሉ ተስፋ ላደረጓት ፣ ለሰው ልጆች የድኅነት ምክንያት ለሆነች ለድንግል እናቱ ለአንዱ ደቀመዝሙር የሰጠውን ቃል ኪዳን እንኳ አልሰጣትም ብሎ ማሰብ የሚዘገንን ነው ። የእመቤታችን ቃል ኪዳን የተጀመረ ጌታ ካረገ በኋላ ሳይሆን አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ ነው እግዚአብሔር ለአዳም ''ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሐለሁ'' ባለው ጊዜ እመቤታችንን ለአዳምና ለዘሩ የድህነት ምክንያት ፣ የተስፋ ስንቅ አድርጎ ሰጥቶታል ። (ኢሣ. ፩፡፱)

አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ''አዳም ከገነት በተሰደደ ጊዜ ተስፋው አንቺ ነሽ'' በማለት ገልጿል ። አዳምም ነቢይ ስለሆነ ይህን አውቆ ለሚስቱ ሔዋን ብሎ ስም ከማውጣቱም ሌላ ሔዋንን ሕይወቱ ነሽ ይላት ነበር ምክንያቱም እመቤታችን ከእሱ አብራክ ከእሷ ማኅፀን እንደምትወለድ ስላወቀ ነው በማለት መቅድመ ተአምር ገልጿል ። በአሪት የተጠቀሱት ኪዳን አበው ሲመረመሩ በውስጣቸው ስለእመቤታችንና ስለጌታችን የተነገሩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል ። በአሪት ስለእመቤታችን ቃል ኪዳን ከተጻፉት ውስጥ በመዝ.፻፴፩ ፲፫—፲፯ ላይ ''እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና

ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና እንዲህ ብሎ ፤ ይህች ለዘለዓለም ማረፊያዬ ናት መርጫታለሁ በዚች አድራለሁ እሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ ካህናቶችዋንም ደህንነትን አለብሳቸዋለሁ

ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል'' ይላል ጽዮን የተባለችው እመቤታችን እንደሆነች ከዚህ በፊት በዚሁ መጽሔት በስፋት ስለተገለጸ ትርጓሜ ውስጥ እንገባም በመዝ. ፹፮ ፡ ፩—፯ ላይ ደግሞ ''. . . ሰው እናታችን ጽዮን ይላል በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱ ልዑል መሠረታት እግዚአብሔር ለሕዝቡ በውስጧም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል በአንቺ (ቃል ኪዳን አማላጅነት) የሚኖሩ ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል'' ይላል ።

በዚህ መሠረት ከተመረጡት ሁሉ የተመረጠች ከተቀደሱት የተቀደሰች እመቤታችን ጌታችን ካረገ በኋላ ወደልጅዋ መቃብር በየዕለቱ እየሄደች ስለሰው ልጆች ስትጸልይ በየካቲት ፲፮ ቀን በወንጌል እንደተጠቀሰው ስሟን ለሚጠሩ በስሟ መታሰቢያዋ ፥ ለሚያደርጉ በጸሎቷ በቃል ኪዳኗ ለሚማጸኑ በልጅዋ ቸርነት ለሚማጸኑ ክርስቲያኖች ሁሉ የማይታበል ቃል ኪዳን ሰጥቶአታል ጌታችን ለእናቱ የሰጣት የምህረት ቃል ኪዳን እንደክብሯ መጠን ለሌሎች ቅዱሳን ከተሰጣቸው ቃል ኪዳን ከፍ ያለ ነው ምንም እንኳን ለወዳጆቹ ሁሉ ቃል ኪዳን ቢገባ የእመቤታችን ግን የቃል ኪዳን ፍጻሚያቸው ነው ።

ስለዚህም ''አልቦ ጸሎት ወአልቦ ትንባሌ ዘእንበሌኪ ማርያም ዘየአርግ ሉዓሌ'' ተብሏል (ትርጉም) ማርያም ሆይ ማንኛውም ጸሎትና ምልጃ ያለ አንቺ ወደልዑል እግዚአብሔር አያርግም ማለት ነው ። በዚህ ምክንያት በተሰጣት የምህረት ቃል ኪዳን ''ኪዳነ ምህረት'' ተብላ ትጠራለች ።

እንግዲህ ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ ሆነው በምድር (በአጸደ ሥጋ) ሳሉ በጸለዩት ጸሎት በተቀበሉት ቃል ኪዳን ያማልዳሉ የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን ያሳስቡልናል እንላለን እንጂ በነፍስ መውደቅ መነሳት ወይም ማልቀስ . . የለባቸውም ቅዱሳን በቃል ኪዳናቸው እንደሚያድኑና እኛም የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን በማሳሰብ መለመን እንደሚገባን ሌሎችንም ርዕሶች በሚቀጥለው እትም ይዘን እንቀርባለን ።

(ይቀጥላል)

**ማሳሰቢያ**

ቁጥር ፩ መለከት ባልደረሳቸሁ ደንበኞቻችን በአድራሻችን ጠይቃችሁ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።